1425. አባፔ ክይድ ጣዛ ላጩስ

. ከአባያ ወጥቶ ጤዛ ይልሳል

.. የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው

1426. አቡዋ ቦረነው ቦሉወው መገኔስ

. አጐቱን ለመስደብ ለአማች ስሞታ ይነግራል

.. በሬ ለማኮላሸት አህያውን ያንከባልላል

.. በአህያ ተከልሎ ጅብ ይወጋል

1427. አቦ ሄ መላው ተ አዝና ግድኤሬኔ ገውሱ ምሽርያ

. ምነው ያ መልከ መልካም ባሌ በሆነ ትላለች ሴትየዋ

.. ምኞትና ጉም አይጨበጥም

1428. አቦ ኔ ዎርዱዋፔ ተነ ኤርሰ ግን ህን ሽወን ጋሽያ ቡክዮጋ

ቤአ ግን ተ አይፍየንከ ሱለይ ጌሊቼስ ጌስ ነአይ

. አብዬ ከውሸትህ አስተምረኝ ቢለው እዚያ ሸዋ ጤፍ ሲያበጥሩ እይ ይለዋል ልጅም መልሶ አይኔ ውስጥ እብቅ ገባ አለ ይባላል

.. ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት ሸንኮራ ሆኖ አይኔ ውስጥ እብቅ ገባ ይላል

1429. አቦ አቤ ገደን ጋሼ ቡኬትን ተ አይፍየን ኡቱለይ ጌሊስ ጌስ

. አብዬ አቤት ቆላ ጤፍ ቢወቃ እዚህ አይኔ ውስጥ እብቅ ገባ አለ ይባላል

.. ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት ሸንኮራ ሆኖ እብቁ አይኔ ውስጥ ገባ አለ

1430. አቦ ደሌጋደን ጤታ ኩንተርከነ ገውሱ ጠለህያ

. ምነው እንደዳሌ መቶ በሞላሁ ትላለች ቆሌ

.. ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ፣ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ

1431. አቱመቴተይ መልአ ዴምን ካት ዶምእየ ጋጩስ

. ብልት ጣፋጭ ነገር ሲያገኝ ፍሬው ይገጫጫል

.. መብል ላሞራ ጩኸት ለቁራ

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

1432. አቱመነይ አለውኔ አዱወውኔ ዩሌቴስ

. ወንድ ልጅ ለጦርነትና ለአደባባይ ነው የሚወለደው

.. ወንድ ልጅ ለፈረስ ሴት ልጅ ለበርኖስ

1433. አትኮ አሴነአ አይቄትከ ከይሴ ነአ

. ከተረፍኩ የሴትየዋ ልጅ ከተያዝኩ የሌባዋ ልጅ

.. ሰግቶ አይሞቱም ታሞ ነው እንጂ

1434. አቹይ በይነ ኩትያ በንጋ ሙምያ ምተውሱ

. ጥርስ የሌላት ዶሮ ገብስ እንዳለ ትውጣለች

.. ችግር ብልሃትን ትፈጥራለች

1435. አቹይ በይነ ኩትያ ግለ በንጋ ውርሰውሱ

. ጥርስ የሌላት ዶሮ የሰፈድ ገብስ ትጨርሳለች

.. ጉድ ይገርማል አህያ ከጅብ ይከርማል

1436. አቹይ በይናረ አቹይ ዴእዮሮ ሰጠ ቢሰውሱ

. ጥርስ የሌላት ጥርስ ያላትን ነክሳ ታሳያለች

.. አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ፣ ሄዳ ታሸታለች የድመት አፍንጫ

1437. አቹይ ናአሽን እሱዋ ምጥለይደ ኬሰውሱ

. ያላት ጥርስ ሁለት ነው ግን አንዱን ጤቅ ስትልበት ታወልቃለች

.. ሲ.ጋጌጡ ይመላለጡ

1438. አቻ አግድ ቡቻ ሜንትያ ዛለ ሃልታ አዋ አግድ ነአ ዎርያ ሀርጌ ሀጣታ

. ጥርስ ትቶ አገጭ የሚሰብር የአለት ድጥ አባት ትቶ ልጅ የሚገድል ግፈኛ በሽታ

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

.. አያድርስ ነው

1439. አነቀይ ሀድርሰን ቶርን ዎዴነይ ኡሸቸን ሾዴነ

. ኃይለኛ በግራው የወጋውን ደካማው በቀኙ አይነቅለውም

.. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

.. አንድ ሰኔ የገደለውን ሶስት ሰኔ አያድነውም

1440. አንኡ አይያ ቡንአ አይዮ ጎቸውሱ

. የአንአ እናት፡የቡንአን እናት ትንትታለች

.. ከእጅ አይሻል ዶማ

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

1441. አንካ ቀንጥን ሎሎይ ቃጤስ

. ብሳና ሲቆርጡት አሽቃሞ ይነቃነቃል

.. አብ ሲነካ ወልድ ይነካል

.. ነግ በኔ

1442. አንዝ ዴእሽን አሹዋ ሚቴስ

. እዳ እያለ ስጋ ይበላል

.. ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም

1443. አንዶ ባነው ጌንዶ ዎዴስ

. አንዶ (ቦታ) ለመሄድ ጌንዶ (ቦታ) ይወርዳል

.. ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

1444. አንጎት አሰራ ማይዮጌኔ ጌኔስ ጉልአ ዱትዮጌ እሱዋ ጌስ

. አንጎት (ዘር) ጥብቆ መልበስና የሚዳቋ እትብት መጣል አንድ ነው ይባላል

.. ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ መመለሻ የለውም

1445. አኬች ዋሱዋ መራየ ስዩፑ

. ጥጃ የሞተባትን ላም ጩኸት ጥጃ ያላት ላም ጆሮ አይስማ

.. ጆሮ ደግ ይስማ

1446. አኬክድ ጬልን ከስቶልያ አይፌ ቤቴስ

. አተኩረው ካዩ የቁንጫ አይን ይታያል

.. ውሃ በለዘብታ ድንጋይ ይፈነቅላል

1447. አኬኬነ ጉፌይ ተካሬነ ሱይልያ ሜንቴስ

.. ያልታሰበ ዝላይ ቅልጥም ይሰብራል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

1448. አኬኬነ ጌሬሰይ ዛርሽን ሜቴስ

. ያልታሰበ ቀረርቶ ለመመለስ ያስቸግራል

.. ሳያውቅ የተረተ ሳይዘራ ያመረተ

1449. አኬኬነን ጉፓደይ ኮሌነሳፔ ሜቂስ

. ሳያስብ የዘለለ ከማይጠገንበት ይሰበራል

.. ሳያውቅ የተረተ ሳይዘራ ያመረተ

1450. አወን ሾጮ ከነይ በደለ ሙሰን ሃይቂስ

. በፀሐይ የተመታ ውሻ በበቆሎ እሸት ጊዜ ይሞታል

.. በክፉ ዘመን አጐንብሶ ይሄዳል

.. ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ

1451. አወን ጎደርያ ቤእደ ከነይ አግነን ኩዋ ቤእድ በቀቴስ

. ቀን አውሬ ያየ ውሻ የጨረቃ ጥላ አይቶ ይሮጣል

.. እባብ ያየ በልጥ በረየ

1452. አወን ኦቴናጌ አግነን ውቂስ

. በፀሐይ ብርሃን የማይሰራ በጨረቃ ይሰርቃል

.. ጊዜ ያለው ጊዜ አይጠብቅ

.. በጊዜ መስራት ያኮራል

1453. አዋቅያ ሻሮንተ መችያ አዝና ሞጉዋ ድገውሱ

. ልታይ ባይ የሻሮ ሚስት የባሏን ቀብር ትከለክላለች

.. የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም

.. አወቅሽ ቢሏት መጽሐፍ አጠበች

1454. ኣዋቅያ ኤቴሮና መጫስያ ኣዝና ቀቸ ወይውሱ

. የቀበጠች የኤቴሮ ልጅ ሚስት ባሏን አስራ ትደበድባለች

.. የጠገበ ሰው ራሱን አያውቅም

1455. ኣዋቅያ ፐርሶይ ጉሩርየን ከኤስ

. የአወቅሁ ባይዋ ጠላ በትንሽ ቅል ይበስላል

. የቀበጧ ጠላ በትንሽ ቅል ይፈላል

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

1456. ኣዋቅያ ፐርሶይ ጩሩርየን ከኤስ

. የቀበጥ ሴት ጠላ በጮጮ ይበስላል

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

1457. ኣዋቂ ምሽርያ ተ እቾሹ እራሻ መቾ ገውሱ

. አፈኛ ሴት የአምስት ዳኛ ሚስት ነኝ ትላለች

.. ለእብለት ስር የለው ለእባብ እግር የለው

1458. ኣው ምጠይ ግን ካት ደጉዋ፣ ያትን ኔነ አይብ ምጥሲ ግን

ኤተ አያነይ ምጥሴስ

. የት ትሮጣለህ ቢሉት የንጉስ ደቦ፣ ታዲያ ምን ያስሮጥሃል ቢሉት ውቃቢያቸው ያስሮጠኛል

.. ላለው ቅንጭብ ያረግዳል

.. ፈሪ ለናቱ

1459. ኣው ምጥንከ ሀይቆይ ኣቴና የዮፕ

. የትም ብትሮጥ ሞት አይቀርምና አትፍራው

.. የማይቀር እዳ የሞት እንግዳ

.. ሞት አይቀርም ስም አይቀበርም

1460. አው ዱልየው ጩርቅ ባወሽን መላዮ ዎሴስ

. ለቂጡ ጨርቅ የሌለው ደህና ያባብላል

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

1461. አውቃል ገይ አድሳበ ጌልን አላቁም ገይ አጎና ዛላፔ ስሜስ

. አውቃለሁ ያለ አ.አ ሲገባ አላውቅም ያለ ከነአጐ ወንዝ ይመለሳል

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ

.. ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል

1462. አውድየን ሞይ አሱር ገቴስ

. በአውድማ ላይ የበሉት አሱራ የሚባል ቦታ ያደርሳል

.. የገባ ያገለግላል

1463. አዘለ አዝነይ ሸሃረ መጫስዮ ኤኬስ

. ሰነፍ ባል ነፍሰ ጡር ሴት ያገባል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

1464. አዘለ አዴ ዎዴጠ መጫስዮ ኤኬስ

. ሰነፍ ሰው እርጉዝ ሴት ያገባል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

1465. አዘለይ ሰንበተን ኦቴስ

. ሰነፍ በሰንበት ቀን ይሰራል

.. የፋቂ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ አንዱን ይዘፍቅ

1466. አዘለይ ሸየን ሼምፔስ

. ሰነፍ አር በማራት እረፍት ያደርጋል

.. ለሰነፍ የጠገበበት ያደረበት ይመስለዋል

1467. አዘለይ ቢታ ኦት ቤነሽን ጎተራ ኤሴስ

. ሰነፍ መሬቱን ሳያርስ ጐተራ ያቆማል

.. ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ፀስከምቢያው ቁጢጥ

1468. አዘለይ ኮታ ኩንትኮ ጎሻ በሼስ (አጌስ)

. ሰነፍ ጐተራው በእህል ከሞላ እርሻ ማረሰን ይተዋል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

1469. አዘላ ሽየይ ሱቁዋረ ውሬስ

. የሰነፍ ሰው አር በፈስ ያልቃል

.. ሰነፍ ቢመክሩት ውሃ ቢወቅጡት

1470. አዘላ ሽየይ አዱሶ

. የሰነፍ አር ረዥም ነው

.. ሰነፍ በአል ያበዛል

1471. አዘላ ቶመይ ዱቡሽን ሜቂስ

. የሰነፍ ሰው ጦር አደባባይ ላይ ይሰበራል

.. አያድን ጋሻ ቂጥ ያስወጋ

1472. አዘላ ኦሶይ ሜቶን ገቴስ

. የስንፍና ስራ ችግር ላይ ይጥላል

.. ሰነፍ ሰው ያሰንፋል

.. ሰነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል

1473. አዘላ ኩሼ ባታ ጌሌነ

. የሰነፍ እጅ ጋን ውስጥ አይገባም

.. መርፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም

1474. አዘልያ በኡዋረ ሽየውሱ

. ሰነፍ ሴት እንዳዘለች ታራለች

.. ሰነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል

.. ይሉኝ አይል የጓላውን አያይ

1475. አዝነይ ሀይቀነው ሃንሽን አቸይ ቀሬቴስ

. ባል ሊሞት ሲል ጥርሱ ያምራል

.. የሚሞት ልጅ እንገቱ ረዥም ነው

.. የማታድግ ጥጃ እናቷን ትመራለች

1476. አዝነይ መችዮ ዴሜነን ገልባ ሂጤስ

. ሰውዬው ሚስት ሳያገኝ ቁርበት ያነጥፋል

.. ወጥ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ

1477. አዝነይ ሲቅዮ መችዮ ሙለሌ ጩሌስ

. ባሏ የሚወዳትን ሚስት ለጋ ዱባ ያንቃታል

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

1478. አዝነይ ሲቅዮ መጫስዮ ጀበነይ ዴጤስ

. ባሏ የሚወዳትን ሚስት ጀበና ይከብዳታል

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

1479. አዝነይ ታጋ ኦይዳወይ

. ባል ማለት የኔ ነው አራት ያለው

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

1480. አዝነይ እጥዮ መችዮ ሹቸይ ጡቤስ

. ባል የሚጠላትን ሴት (ሚስት) እንቅፋት ይመታታል

.. የተከፉ ተደፉ

.. ጊዜ ሲከዳ መሬቱ ያድጣል

1481. አዝነይ እጥዮ መችዮ እፍተይ ዎሬስ

. ባል የጠላትን ሴት መዝጊያ ይገላታል

. የተከፉ ተደፉ

1482. አዝነይ እጥዮ መችዮ ጩቸይ ጦቀርሴስ

. ባል የጠላትን ሚስት ቅማል ይረግጣታል

.. ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለእዳ አይቀበለውም

1483. አዝነይ እጥዶ መችዮ ሀሙሰ ግየይ ኤሬስ

. ባል የጠላትን ሴት የሀሙስ ገበያ በሙሉ ያውቃል

.. ጊዜ ሲከዳ መሬት ያዳልጣል

.. ሰድቦ ለሰዳቢ

1484. አዝነይ ኤኬነ አምኤ፣ ኤክን ቆሜነ ወኤ

. ባል የማይፈልግሽ ቦዝ ቢያገባሽም የማታቅፌ ፈዛዛ

.. የሰው ቃሪያ እስቲሞት ድረስ አይበስልም

1485. አዝነይ አይችዶ ዱርጋሊዮ ጊያን ቃቼስ

. ባለጌ ሰው የሰውን እጮኛ ገበያ መሀል ይጠይቃል

.. አፈ ሰፊ ሰው የምግብን ጣዕም አያውቅም

.. ባለጌን ካሳደገ የገደለ ይፀድቃል

1486. አዝና ቤአቤኡኩሽን ዜርየን ሂጣ ዬገውሱ

. ባሏን ሳታይ ደፍ ላይ መኝታ ታነጥፋለች

.. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል

1487. አዝና ጭምየ መችያ ሼንዴረን ሼሌሰውሱ

. ባሏን የምታታልል ሚስት በገንፎ ታንደላቅቀዋለች

.. ሊበሉ የፈለጉትን አሞራ ይሉታል ጅግራ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

1488. አዝናስ ዎርዶትደ መጫስያ ብድንተን ዝንአውሱ

. ለባሏ የምትዋሽ ሴት አመድ ላይ ትተኛለች

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

1489. አዝናኔ ግያኔ ጌልድ ቤኤቴስ

. ባልን አግብቶ፣ ገበያን ገብይቶ ማየት

.. ያየ ይፈርዳል የሰማ ይናገራል

1490. አዝን ኪክሰ፣ ክንች ወድድ ኪሴተ አይሳ አጭያጌ ገውሱ ኤጩርያ

. ባል ማለት ኪኪሳ ነው እንክትክት አድርጉ ደብድቦ በንጤት ቅቤ የሚጠግን ትላለች አይጢት

.. የባል ደግነቱ ባትናገር ሚስቱ

1491. አዝከ ጊደይ ዶርሰ አጮቴስ

. ወስከ ያለ የበግ ባለእዳ ይሆናል (በግ ይከፍላል)

.. ሚያ ባልኩ ፍየል ከፈልኩ

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ

1492. አያነይ ኬህን ማጣነይ ዎሬስ

. እድል ሲቀና በአጋሰስ ይገደላል

.. እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ

.. እድላም አሞሌ በቅሎ ይለውጣል

1493. አያነይ ይን ሜጩተነ ጊሽን አጡመይ ቆርያ ገኪስ

. ውቃቢ አምላክ ሲቀርብ እታጠባለሁ ሲሉ እድፍ አንገት ይደርሳል

.. የማትሄድ መበለት ዞራ ዞራ ትሰናበት

.. ጊዜ ወርቅ ነው ግን ሃላፊ ነው

1494. አይ ሞ ግየ ጎደሬኔ አሃ ዘልአየ አብጤኔ ቦድቴን ገይቶሶነ

. ምን ልብላ የሚል ጅብና ሬሳ የሚነግድ አብጤ ቦዲቴ ይገናኛሉ

.. ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ

1495. አይ ሞ ግያረ አውረ አው ቦ ግየጋረ ገይቶሶነ

. ምን ልብላ የምትለው የት ልሂድ ከሚለው ጋር ይገናኛሉ

.. ቂጢኛም ከውርዴ ይዞራል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግብ

1496. ... አሾይ ባወ ቀይጣርያው ቦንቆይ ባወ

. ለአገልጋይ ይሉኝታ የለውም ለጭራሮ ፍም የለውም

.. ከይሉኝ አይል አይብ አትብላ

1497. ... ናቴ ቂማ ውቄስ

. ባሪያ የልጆችን ምግብ ይሰርቃል

.. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል

1498. ... አሎይ በሌ ዎንቴታ

. የባሪያ ለቅሶ በቀብር ማግስት ነው

.. ከሌለህ የለህም

1499. ... ጰጥራሮይ በሌ ዎንቴታ

. የቀበጠች አገልጋይ በቀብር ማግስት ሙሾ ታወርዳለች

.. የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም

1500. ... ዎዘናን ሀንተይ ዴኤስ ሃሪያ ዎዘናን ሱረይ ዴኤስ

. ከባሪያ ልብ ውስጥ የቅቤ እር አለ፣ አህያ ልብ ውስጥ ሰርዶ አለ

.. ዶሮ ብታልም ጥሬዋን

1501. ... ማድየበ ድምኮ መይድያ ቆተውሱ

. አገልጋይዋ ረዳት ሲመጣላት መጅ ትደብቃለች

.. ልርዳሽ ሲሏት መጇን ደበቀች

1502. አይበ ዱረይ ግን አፈለይ ቴቆሮ ቢአርኪ ገውሱ

. እንዴት ትጨፍራለች ቢል ልብስ አጥታ እቤት የዋለችውን ባየህ ትላለች

.. አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል

1503. አይብ ገትን ጢፊግ ቱሺ ግ

. በምን የተነሳ ነው በከፋይ (በትንታግ) የሚጠብሰው

.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ

1504. አይቤ ገይ አላድያ ቀንጤስ

. ምንድነው ያለ አላድ ይከፍላል

.. ሚያ ባልኩ ፍየል ከፈልኩ

1505. አይቤ ግየ ግምራኔ አይ ሞ ግየ ጎደርያኔ አይቤ ገትደይ?

. ምንድነው የሚል የጊሚራ ሰውና ምን ልብላ የሚል ጅብ ምን አገናኛቸው?

.. እግር ሲሳሳት ከአንጋዳ አፍ ሲሳሳት ከእዳ

1506. አይኔ ዴእንከ ሀይቆይ አቴነ

. ምንም ቢኖር ሞት አይቀርም

.. የማይቀር እዳ የሞት እንግዳ

1507. አይኮ በይነ መንቆይ ቦተ ኤሳ ዎተይስ ጌስ

. ምንም የሌለው ድሀ ነጭ ማር እሰጥ ይላል

.. ቢከፍቱት ተልባ

.. አስመሳይ

1508. አይኮ እሜነይ ኣሰ ኬጠ ጌስ

. ምንም የማይሰጥ ቤት ሰፋ አድርገህ ስራ ይላል

.. በቅሎ ግዙ ግዙ አሞሌ ላያግዙ

1509. አይፍያ ገሄቴነ ቦሎይ ሞቶን ገይቴስ

. ምላሽ ያልተጠራ አማች ሙግት ቀን ይገናኛል

.. ዱብ እዳ ነው

.. ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

1510. አይፌ ጤል ከልድ ሰኬቴስ

. አይን አይቶ ሲጠግብ (ሲያበቃ) ይታመማል

.. ያልፈሳንበት ዳገት የለም አለች እንስሳዋ

.. ሲበዛ ማር ይመራል

1511. አዱሰ ኩሼ ሄዘንታ ቆሜስ

. ረዥም እጅ ሶስተኛ ሰው ያቅፋል

.. አፈ ሰፊ ሰው የምግብ ጣዕም አያውቅም

1512. አዱሰ ደንጮይ አዝነን ገቴስ

. ረዥም መቀነት ለባል ያበቃል

.. የመንገድ ረዥም እድሜ ያረዝማል

1513. አድያ አይፍያ ቶይሰይ ጋሼ

. የሽማግሌውን አይን ያጠፋው ጤፍ ነው

.. ሲበዛ ማር ይመራል

1514. አዲሌ ከንያ አዝና ቤአደ ዎጠውሱ

. የስሪያ ውሻ ባሏን አይታ ትሮጣለች

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

1515. አዴ ሀይቀናንድ ዱንያ ክዩስ

. ሰውየው ሊሞት ሲል ተራራ ላይ ይወጣል

.. አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ ፤ ሄዳ ታሸታለች የድመት አፍንጫ

1516. አዴ ኩቱዋ ጎደይ ጋሽ ገድያ ጊሬስ

. አንድ አውራ ዶሮ ያለው ሰው ጋሻ መሬት ይገብራል

.. ከማን አንሼ

.. የቶክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

1517. አዶይ ብድንታ ታውሌ ጌስ

. የቦሌ አፈር አመድን አባዩ ይላል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

.. እርስ በርሱ ስጋን ጠበሱ

1518. አገ እጠይ በንገ እጤስ

. ተውን እንቢ ያለ ገብስ እንቢ ይላል

.. ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው

.. ሲመክሩት የማይሰማ ሲመትሩለት የሚከሳ

1519. አገ ዎረደ ጌሬረ

. ተው ገድለህ ፎክር

.. ሳይገድሉ ጐፈሬ ሳያረጋግጡ ወሬ

.. ከመጠምጠም መማር ይቅደም

1520. አገ ግን እጥደይ ዋዩስ

. ተው ቢሉት እንቢ ያለ ይቸገራል

.. ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው

1521. አጋረ ዴእሽን ገንታረ ገለተ ኤከውሱ

. የጠመቀች አያለች ያቀመሰች ትመሰገናለች

.. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ

.. ያረሰው በሬ እያለ የሚነው አህያ ይመሰገናል

1522. አግነን አይስ ጦምፐይ ግን ሃ ፖአ ጋደ እተይስ ጌስ ጌቴስ

. በጨረቃ ለምን ታበራለህ ቢሉት የበለጠ ይብራ ብዬ ነው አለ ይባላል

.. ላለው ይጨመርለታል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

1523. አግነን ደሀናረ አወን የሼስ ገውሱ

. በጨረቃ የምትኮበልል ቀን ፈራሁ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

1524. አግነን ጕደሬ ዩዴትዶ ከነይ ገለስ ከሬ ክዩን

. በጨረቃ ጅብ ያባረረው ውሻ ቀን ውጭ አይወጣም

.. እባብ ያየ በልጥ በረየ

1525. አጌነንተሶ አይያ ፐርሱዋ መልኡዋ አገውሱ ግን ማታ ወለከውሱ

. የነአጌና እናት ጣፋጭ ጠላ ትጠምቃለች ብትባል ወተት ትበርዝበታለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቂስ ሚስት ዳዊት አጠበች

1526. አግነኔ አው መቾኔ አመኔቴን

. የጨረቃ ብርሃንና የእንጀራ እናት አይታመኑም (አያስተማምኑም)

.. የጣውንት ደግ የእንቧጮ ዘንግ የለውም

1527. አግና ፖኡዋኔ ሀርያ ሞዱዋኔ ተ ኤረይስ ጌስ ኻደሬ

. የጨረቃን ብርሃን ድምቀትና የአህያን ስባት እኔ አውቃለሁ ይላል ጅብ

.. የወጥን ጣዕም ቀላዋጭ ያውቃል

1528. አግን ዴእያረ አልን ዴእያገ ጌለውሱ

. የተናቀች የተጠላን ታገባለች

.. ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል

1529. አጣሬ ጡራ አድን ጉታ ቀንጤስ

. ልኳንዳ አራጅ ችግር (ምስጢር) ቢነግሩት ትንሽ ይቆርጣል

.. ያንዱ ችግር ላንዱ የእንጀራ ልጅ ነው

1530. አጥራሮይ ፐራ ማጣና ኬሴስ

. የሚቀብጥ ፈረስን ጌኛ ያስመስላል

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

1531. አጬዋ ቀንጤነ ብተኔ ለንጥያ ላፑን ሸሉዋ እመነ ጊድ አሄስ

. እዳ የማይከፍል ሰው ሰባት ማግ እሰጣለሁ ብሎ ጣፊያ በዱቤ ይወስዳል

.. የፈተኛው ያገሳታል በላይ በላዩ ያጕርሳታል

1532. አጮይ በይነ መንቆይኔ፣ ሀርጌ በይነ ግልቀይኔ እሱዋ

. እዳ የሌለበት ድህነትና ህመም የሌለበት ክሳት አንድ ናቸው

.. አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት፣ ጦም ውሎ ጦም አድሮ ጥሩ መሸመት

1533. አጮይ በይነ መንቆይኔ፣ ጕሜ በይነ ግልቀይኔ ፐጤነን አጌና

. እዳ የሌለበት ድሃና ሃጢአት የሌለበት ክሳት ሳያልፍላቸው አይቀርም

.. ለሁሉም ጊዜ አለው

.. ቀን ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል

1534. አጮይ በይነይ ቱሞ ተልኤስ

. እዳ የሌለበት ነጭ ሽንኩርት ይበደራል

.. ሳይቸግር ጤፍ ብድር

1535. አጮይ አጬዋ ቀንጤስ

. እዳ እዳን ይከፍላል

.. እሾህን በእሾህ

1536. አፈል በይነ አሽከ ኬት በይነ ፖችታ ጌለውሱ

. ልብስ የሌላት አሽኬ (ስም) ቤት የሌለውን ቀትረ ቀላል (ከላባ) ታገባለች

.. ቂጢኛም ከውርዴ ይዞራል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

1537. አፋማ ሰምፓ ነእዮ ከምባታ ግላ ነአይ ኤኬስ

. የአፋማን የሰፌድን ልጅ የከንባታ የእህል መንፌያ ልጅ ያገባል

.. ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል

1538. አፍል አወ አቴስ፣ ነምስ ነአ ኡዴስ

. ልብስ አባት ያደርጋል ረሃብ ልጅ ያደርጋል

.. እህል ለቀጠና ወርቅ ለዝና

.. ሆድ የኔ ነው ሲሉት ቁርጠት ሆኖ ይገላል

1539. አራ ከዎይ ባንጋ ም ኤር ግን ጫድዮ ኡዱለይ አውኔ ጌስ

. የአራ ንጉስ ገብስ በልቶ ያውቃልን ቢለው ገብስ የሚወቀጥ በት ሙቀጫ የት ሆነና ይላል

.. ለቀባሪ አረዱት

1540. አተ ሎይተይስ ጋደ ፐላ ጢጠ አተውሱ

. አሳመርኩ ብላ አይብ ጠብሳ ታቀርባለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ሲሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

1541. ኣተ ኣሌቅዳረ ኤየ ጌለውሱ

. ኣብዝታ የምትኳል ሞኝ ታገባለች

.. መራጭ ከምራጭ ላይ ይወድቃል

1542. ኣተ ኤረይስ ጋደ ፐላ ጢጠ ኣተውሱ

. አውቃለሁ ብላ አይብ ጠብሳ ታቀርባለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሐፍ አጠበች

1543. ኣት በነሃ ደሮይ ሀረ ሸያ ኤሄስ

. ብዙ ማማጥ ሌላ አር ያመጣል

.. አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

1544. ኣት ደውሮ ባነ ጊድ ጨዬጌስ

. ኣታ ዳውሮ ኣገር እሄዳለሁ እያለ ያረጃል

.. መሄድ መሄድን እያደራጀሁ እንደ ጉሬዛ ከቤት አረጀው

1545. ኣክን ግዴነ ፤ ኣይፍድ ግዴስ

. ስፋት ሳይሆን ምርት ነው የሚያጠግበው

.. ከብዛት ጥራት

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

1546. ኣኮይ ተ ኣዝና ኣሆይ ተ ቆልኡዋ፤ ግዱወን ዴእየ ኔነ ኣሰፉ ኣይብ ገቲ?

. ኣኮ ባሌ፤ ነፈው የኔ ጉያ ነው በመሀል ኣሰፉ ኣንተን ምን ያገባሀል?

.. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ

1547. ኣወቴተይ ኣዴቴተ

. ኣባትነት እርጅና ነው

.. ኣባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው

.. እድሜ ለንስሐ ዘመን ለፍስሐ

1548. ኣወን በይነ ሣጋዮይ ነኣስ ጌዴ ሜንቴስ

. በአባት የሌለ አልቦ የልጅየውን እግር ይሰብራል

.. አባቱ ያልበላው ኑግ ልጁ አማረው ቅባኑግ

1549. ኣወን በይነ ቶገይ ኣፉወን ዩጌስ

. በአባት የሌለው በቅሎ ላይ መቀመጥ ገደል ይከታል

.. አያውቅ ቢዳኝ ከቤቱ ይናኝ

.. ያላባቱ ቢዙቁን አባክኖ ያባክን

1550. ኣወን አንጀትደ ነኣይ ዱቡሽን ፔኤስ

. አባት የመረቀው ልጅ አደባባይ ይውላል

.. አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው

1551. ኣወይ ሲቅዮ ነእያ ሰዎተውሱ፣ አገነይ ሲቅዮ መችያ ሉፈተውሱ

. አባት የሚወዳት ልጅ ጋለሞታ ትሆናለች፣ ባል የሚወዳት ሚስት ትኮላተፋለች

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

1552. ኣወይ በርዮ ኣሱዋ ሚድ ናተ ሆአ ጌስ

. አባት ለራሱ ስጋ እየበላ ልጆቹን እንዳይበሉ ያስፈራራል

.. ስሱ አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

.. እኔ ልብላ አንተ ጦም እደር

1553. ኣወይ በው አሹዋ ሚድ ነኣ ተማ ሆአ ጌስ

. አባት ለራሱ ስጋ እየበላ ልጁን እሳት ሙቅ ይላል

.. የጠገበ ሰው የተራበውን አያውቅም

1554. ኣወይ ኩቱዋ ሸምን ነኣይ ገወራ ሸሜስ

. አባት ዶሮ ሲገዛ ልጅ ድመት ይገዛል

.. የሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ

1555. አወይ ዜብድ ዛርዮ ሰሁዋ ነአይ ጎይድ ገቴን

. አባት በድድቅ አርሶ የሚያደርስበትን ቦታ ልጅ አርሶ አያደርስም

.. ወይፈን ካረሰው በሬ ያንከላወሰው

1556. አወይ ዩል ኡይን ነአው ዶነይ ሰዌስ

. አባትየው በርዞ ቢጠጣ የልጁ አፍ ይሸታል

.. አቃቢት በተልባ በበላችው መነኩሴውን ተጋረፈው

1557. አወይ ደረናፔ ቃደይ ደሮ

. አባት ከሚበልጥ እድል ይብለጥ

.. ጊዜ ነው እንጂ ቁም ነገራም ባላባትነት አያኮራም

.. እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ

1558. አወይ ዴእሽን ሃረ፣ አወይ ዴእሽን ዎጠ

. አባት እያለ ንብረት አፍራ፣ ጀምበር እያለች ሩጥ

.. አባት እያለ አኪጥ ጀምበር እያለች ሩጥ

1559. አወይ ዴእሽን ነአይ ዳነቴስ

. አባት እያለ ልጁ ይሾማል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

1560. አወይ ጠመታ ክይሶትን፣ አን ክርያ ናገኔ

. ባለቤት ትኩስ ወተት ከሰረቀ፣ ቤቱን ማን ይጠብቃል

.. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል

.. የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማድ

1561. አወይኔ አይያኔ ተመ አቾን ሃሰይዶጋ ነአይ ሄንተ ገዴ ኬሴስ

. አባትና እናት እሣት ዳር የተናገሩትን ልጅ ከብት እሚያግድበት ቦታ ያወጣል

.. ልጅ ፊት ምስጢር አታውራ

1562. አዋ መጫስያ አዝና ናተ ጨለይደ ማታ ብድንተን ጥገውሱ

. የእንጀራ እናት የባሏን ልጆች እያየች ወተት አመድ ላይ ታጠላለች

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

1563. አዋ ሚደ ቦረነይ ነአይ ዎቃ ግድዴ ጌስ

. አባቱን የበላ ጭራቅ ልጁ ምን አከለ ይላል

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

1564. አዋ ቢተይ አሰራ መይዝን አሰ ቢተይ አፈለ መይዜስ

. ያባት አገር ጥብቆ ሲያለብስ የሰው አገር ሸማ ያለብሳል

.. እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል

.. ያልተገላበጠ ያራል

1565. አዋ ቤኤነይ መይዛ ላሞቴስ

. አባቱን ያላየ ቅድመ አያቱን ይናፍቃል

.. በቅሎ አባትህ ማነው ቢሉት ፈረስ አያቴ ነው አለ

.. አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቀ

1566. አዋ ኤሬነይ በ ኮቸን ጫቂስ

. አባቱን የማያውቅ በዘሩ ይምላል

.. በቅሎ አባትህ ማነው ቢሉት ፈረስ አጎቴ ነው አለ

1567. አዋ ከርየ ሼሸይ ሂተን ዬስ

. ባለቤቱን የሚንቅ ሽንት መኝታው ላይ ይመጣበታል

.. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ

1568. አዋ ከሪደ ጩቸይ አፈለን ዎዴስ

. ባለቤቱን የናቀ ምራቅ ልብሱ ላይ ይለጠፋል

.. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁም

.. የባለጌ ምራቅ ከፍ ሲል እደረቱ፣ ዝቅ ሲል እጉልበቱ

1569. ኣዋ ዎረ ቦረነይ ነአይ ዎይሰ ግድዴ ጌስ

. አባቱን የገደለ ቦረና ልጅን ማንን አከለ ይላል

.. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

1570. ኣዋ ዎረነው ኤቅድ አይዮ ሾሎለዩስ

. አባትየውን ለመግደል አስቦ እናትየዋን ያቅለሸልሻታል

.. አባ ኮሶ ጠጥተው አቃቢቷን አሻራት

1571. ኣዋ ዎርደ ማረቆይ ነአይ ዎቃ ግድዴ ጌስ

. አባቱን የገደለ ማረቆ ልጅየው ማንን አከለ ይላል

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

1572. ኣዋስ ምዮበይ ባሽን ነኣስ አቾይ ሞኬስ

. አባትየው የሚበላው የለው ልጅ ጥርስ ያበቅላል

.. እኔ የምበላውን ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ

1573. ኣዋፔ አድደሰ ሃይተይ አሮሞ ገክዴስ

. ከአባትህ የበለጥክ ዝናህ አሮሞ አገር የደረሰ

.. ልጅና ብትር ይቀድማል

.. እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ

1574. ኣው መሱንተይ አሰስ አሾ መለቴስ

. የአንዱ ቁስል ለሌላው ደህና ገላ ይመስለዋል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. ያልተነካ ግልግል ያውቃል

1575. ኣው መችያ አሉኩ አግንያ ሆኡኩ

. የእንጀራ እናት አትገላግልም፣ ጨረቃ አትሞቅም

.. የእንጀራ እናት ምን አጠናሽ እንደጅማት

1576. ኣው መቾ ሃተይ ዱጌን ሚን ፑዴን ኮዩስ

. የእንጀራ እናቱን ውሃ ወደታች ቢወስዳት ወደ ላይ ይፈልጋል

.. ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

.. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

1577. አው ምንን አንክ ኅዱስ

. ባለቤት ቢበረታ የብሳና ሞፈር ያርሳል

.. ከባለቤቱ የዋለ እንቁላል አይሰበርም

1578. አው ሶን ዱእዮ ነእኔ... ሶን ዱእዮ ቱረይኔ እሱዋ

. አባት ቤት ያለ ልጅና ቀጥቃጭ ቤት ያለ ጦር አንድ ናቸው

.. የጋን መብራት

1579. አው ቀንግዶ ነአ ኦኔ አንጀነይ? ጋሺ በይዶሰን አይ ዜረኔ?

. አባት የረገመውን ልጅ ማን ይመርቃል? ጤፍ በጠፋበት ምን ይዘራል?

.. ንጉስ የፈረደበትና ዝሆን የረገጠበት አንድ ነው

1580. አው ቀንጌተይኔ ቱሣ ዘኤተይ እሱዋ

. ያባት እርግማንና የምስሶ መሰንጠቅ አንድ ነው

.. ንጉስ ከተነፈሰ አይን ከፈሰሰ

1581. አው ቃጥን በሌ ቃጤስ

. ባለቤት ሲንቀሳቀስ ለቀስተኛ ይንቀሣቀሳል

.. ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

.. ባለቤት ካልጮኸ ጐረቤት አይደርስም

1582. አው በይነ ነእ ሀርያ ቀኬስ

. አባት የሌለው ልጅ አጉራ ይዘላል

.. አባት የሌለው ልጅ መዝጊያ የሌለው ደጅ

1583. አው አይፌ ቶረ አይፌ

. ያባት (የባለቤት) አይን የጦር አይን ነው

.. ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

1584. አው እሽ ምርጌ አሾ፣ አይ እሽ ምዬ አሾ

. ያባት ወንድም የማጅራት ስጋ፣ የናት ወንድም የሽንጥ ስጋ

.. የናት (ዘመድ) ልጅ የጕን እጅ

1585. አው ዴእሽን ሚሻ አይቴነይኔ አወይ ዴእሽን ሶ ጌሌነይ እቧ

. አባት እያለ ሀብት የማያፈራና ጆምበር እያለች እቤት የማይገባ አንድ ናቸው

.. አባት እያለህ አጊጥ ጀንበር እያለች ሩጥ

1586. አው ዴእሽን ነአይ ፕርዴስ

. አባት እያለ ልጅ ይፈርዳል

.. ይታደሿል እንጂ አይታገሉም

.. ኋላ የመጣ አይን አወጣ

1587. አው ዴእሽን አንጅያ ነአይ ፕጦፖ ጌስ አመቴ

. አባት እያለ ቀድሞ የሚመርቅ ልጅ አይደግ ይላል አመቴ (ሕዝብ)

.. የአባት ባለጌ የበርኖስ አሮጌ የለውም

1588. አው ዶስዶሰን በቄ ዎቴቴስ

. ባለቤቱ በፈቀደበት አስቴ ይተኮሳል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

1589. አውፔ አይያ ሎአ፣ አሾፔ ሜቄት መልአ

. ከአባት እናት ትሻላለች ፣ ከስጋ አጥንት ይጣፍጣል

.. እናት ለልጇ ነቢይ ነች

1590. አውፔ ኤረይስ ጊድ ነአይ እክሴ በጋ ቋጩሶ

. ከአባቱ አውቃለሁ ብሎ ልጅየው በፀጉር በኩል ይፍቃል

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

1591. አውፔ ኤርየይ፣ ፕራፔ ቃጥየይ ባ

. ከባለቤቱ የሚያውቅ፣ ከፈረስ በላይ የሚጋልብ የለም

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

1592. አውፔ ከውይየ አፈለይ ከሴት ዴንዴስ

. ከባለቤቱ የሚቀል ልብስ ቀድሞ ይነሣል

.. የልብስ ቀላል ባለቤቱን ያቀላል

1593. አዎ ተነ ጉሶይ ዎሬስ ግን ተ ዶስዮይ ኦኔ ጌስ

. አብዬ ተቅማጥ ሊገለኝ ነው ቢለው እኔ የምፈልገው ምንድነው አለ ይባላል

.. ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ

.. አታስጐምጀኝ

.. በድንገት አህያ ከጅብ ቤት

1594. ኦይ ሀይቆይኔ፣ ሹቻ ቦለ ኡቴትኔ አቅሸን አቅሸን ኤሬቴስ

. የናት ሞትና፣ በድንጋይ ላይ መቀመጥ እያደር ይታወቃል

.. የናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል

1595. አይያ ተ ኦስ ሙጥሽን ኔ ኦስ ጩሌተይ ገውሱ በነእዮ

. እናት እኔ ለማን እየመተርኩ አንቺ ለማን ትታነቂያለሽ ትላለች ልጇን

.. ሲሰሩለት የማያውቅ ሲሰሩበትም አያውቅም

1596. አይያ ነእዮ ብተውሱ፣ አርሰን ከየ ዝንአውሱ

. እናት ልጇን ታሚርታለች፣ አልጋዋ ላይ ወጥታ ትተኛለች

.. ጠላት ይወጣል ከቤት

.. የናትን ክፋት፣ የደመናን ውሃ ጥማት ባለቤቱ ያውቃል

1597. አይያ ነእዮ ዞረይደ በው ሻረውሱ

. እናት ልጇን እየመከረች ለራሷ ታረግዛለች

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

1598. አይያ ኡንጫ ቶከውሱ፣ ነእያ ጫማ ዎተውሱ

. እናት ቆጮ ትሸከማለች፣ ልጅ ጫማ ታደርጋለች

.. ለናት የሌላት ድሪ የልጅቱን አንገት ይሰብራል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

1599. አይያ ዴእሽን ነእያ ግመውሱ

. እናት እያለች ልጅ ትሽለማለች

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

1600. አይያ ዴእሮረ አይያ በይናሮ ዩሰውሱ

. እናት ያላት እናት የሌላትን ታስለቅሳታለች ይባላል

.. ወገን ያለው ማንም አይታገለው

1601. አዩ ሀይቆይኔ፣ አይዴ ኡቴትኔ ገምእሽን ኤሬቴስ

. የናት ሞትና፣ በርጩማ ላይ መቀመጥ እየቆየ ይታወቃል

.. የናት ሞትና የእግር እሣት እያደር ያንገበግባል

1602. አዩ በጁጌ ጎሶነ ናት

. ወየው ሞንዳላዋ ይላሉ ልጆቹ

.. ወይ ጣጣ ምን ነገር መጣ

1603. አዩ ኢታቴታኔ ፑቶ ዴጦኔ ኤረይ ኤሬስ

. የናትን ክፋትና የጥጥን ክብደት የደረሰበት ያውቃል

.. የደመና ውሃ ጥማትና የናትን ክፋት የሚያውቅ ያውቃል

1604. አዩ ጌስ ሃተይ ኤፍዮ አስ

. ውሃ የሚወስደው ሰው ወየው ይላል

.. ከወደቁ ወዲያ መፈራገጥ ለመላላጥ

.. ከሆነ ወዲያ ንዴት ለሽበት

1605. አዩስ በይነ ሳጋዮይ ነኤስ ኩሽያ ሜንቴስ

. ለናቷ የሌላት አምባር የልጅቱን እጅ ይሰብራል

.. ለናቷ የሌላት አልቦ የልጅቷን እግር ይሰብራል

.. ለአህያ ማር አይጥማትም

1606. አዩስ በይነ ቦርኮተይ ነኤስ ሸይያ ገኬስ

. ለናቷ የሌለ ትራስ የልጅቱን ጆሮ ግንድ ይደርሳል

.. ከኋላ የመጣ አይን አወጣ

1607. ኣዩስ ኦይቀ ዴንድዮበይ ባወሽን፣ ነእያ ሂጠደ ኡተውሱ

. ለናት ይዛ የምተነሣው የላትም፣ ልጅቱ አንጥፋ ትቀመ ጣለች (እናትየዋ ለብሳ የምትወጣው የላት ልጅቱ አንጥፋ ትቀመጣለች)

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

.. ይታደሷል እንጂ አይታገሉም

1608. ኣዩን ጥልቅ ጊድ መሬን ቶልኩ ጌስ

. በእናት ትንሽ ቦታ ታይቶ በልጅ ይጕላል

.. የዘሬን ብተው ያንዘርገዘረኝ

.. ላም በረቱን የሰው ልጅ አባቱን

1609. ኣዩንቶ ዋን ፔእዴት ግን በ ነአ ጩማዳ ኦይካ ኦይኪስ

. እናት እንደምን ዋሉ ቢሉ «ጬማዲ» ልጇን እንደያዘች ይዞኛል ትላለች

.. ክፉኛ ይዞኛል እንጃልኝ

1610. ኣዩጌ እርመተሽን፣ ነኤጌ በንዶ

. የናትየዋ አጣጥ ነው የልጅቷ ግን ጭጉኝ ነው

.. ሊበሉ የፈለጓትን አሞራ ይሏታል ጅግራ

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

1611. ኣደይ ጠልያ ኡይን ገኔስያ ከሬን ሃይቀውሱ

. ኣዳ (ዘር) ኮሶ ሲጠጣ ሚዳቋ አደጅ ትሞታለች

.. ይታደሷል እንጂ አይታገሉም

.. አትሩጥ አንጋጥ

1612. ኣድደ ባልጉወስ ኬታ ኡሴቴነ

. ላለፈው ክረምት ቤት አይቆምም

.. ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም

1613. አድደ ተስካሬ ዮትኮ ሀችስ ቀንኤ ግዴነ

. ስላለፈው ተገዘከር ብናወራ ለዛሬ ቁርስ አይሆንም

.. ላለፈው ክረምት ቤት አይሰራም

1614. አድደ ተስካሬ ዮትኮ ሀችስ ከሆ ግዴኔ

. ስላለፈው ቱገዘካር ማውራት ለዛሬ ራት አይሆንም

.. ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም

1615. አድደጋ ጌለይስ ግያረ.... ጊሴውሱ

. የተሻለ አገኛለሁ የምትል አሽከር ታገባለች

. መራጭ ከምራጭ ይወድቃል

1616. አፉዋ ዶነን ብረስደ ኡስያ ዱፉዋ ዶነን ዩለውሱ

. ገደል አፋፍ የተጠቃች ጊደር መቃብር ላይ ትወልዳለች

.. ጣጣ ፈንጣጣ ድንጋይ ፈለጣ

.. የተከፋ ተደፋ

1617. አፎ ዶነን ሚዛ ሄምየ ናት ጭማ ዋይሶሶነ

. ገደል አፋፍ ከብት የሚያግዱ ልጆች ሽማግሌ ያስቸግራሉ

.. ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም

1618. ኡለታ ዶነን ዎትዲ መለሁዋ ላጬስ

. አልቅት አፉ ውስጥ አስቀምጦ አንገቱን ይልሳል

.. ኖየኋ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

.. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

1619. ኡሉወን በይነበይ ኡሉዋ ሰኪስ

. ሆድ ውስጥ የሌለ ነገር ሆድ ያማል

.. ያልበሉት ዕዳ ያልጠሩት እንግዳ

1620. ኡሉወን ከርዮ ኡረይ ኬሲ ከሬስ

. በሆድ የሚንቁት ሰው ብግልጽ ይንቃል

.. ከሳሹ የተከሳሹን ሆድ ቢያውቅ ኖሮ አደባባይ ባልወጣ ነበር

1621. ኡሉዋ ሀርጌ ከራ፣ ትራ ሀርጌ አጃጅያ

. የሆድ በሽታ ቁርጠት የደረት በሽታ ሳል ነው

.. የኑሮ ፀር ሞት፣ የትዳር ፀር ዝሙት

1622. ኡሉዋ ምሾይ ቁማ ከት ኤሬነ

. የሆድ ውስጥ ትኩሣት ምግብ አያበስልም

.. ሽንበቆ በመርዘሙ ምሰሶ አይሆንም

1623. ኡሉዋ ኤርየ ኩትያ ፐራ ቀከውሱ

. የሆድን የምታውቅ ዶሮ ፈረስ ትረግጣለች

.. ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጪ ታሳድራለች

.. ልብ ያለው አገሩ ሰማይ ነው

1624. ኡሊያ ቡሎ ቦረውሱ

. ድፍርስ ብጥብጥን ትሰድባለች

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

1625. ኡሎ ለጌይ እሻፔ ዳሮ

. የሆድ (የልብ) ጓደኛ ከወንድም ይበልጣል

.. ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጐረቤት ይበልጣል

1626. ኡሎይ ሰክዮ ኡራስ ግየይ ደራ መለቴስ

. ሆዱን ለታመመ ሰው ገበያ ጥሻ ይመስለዋል

.. የተቸገረ ይሉኝታን አያውቅም

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

1627. ኡሎይ ሹቻ ማነ ግን፣ አቸይ ኦናረ ዞሬተደ ጌስ

. ሆድ ድንጋይ እበላለሁ ቢል፣ ጥርስ ከማን ጋር ተማክረህ ይላል

.. ተማክረው የፈሱት ፈስ አይገማም

1628. ኡሎይ ኤርዮ ዮሁዋ አይፌ በር ቀጠነው ጨሌስ

. ሆድ የሚያውቀውን ነገር አይን ለአመሉ ያያል

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

.. ስንተዋወቅ አንተናነቅ

1629 ኡሎይ ዶስየይ ቦይና ኩሼ ኤክዮይ ኡታ

. ሆድ የሚወደው ጐዳሬ እጅ የሚያነሣው አምቾ

. ይሉኝታና ጥቅም አብሮ አይሄድም

1630. ኡሎይ ፔሬትዶጌ ዴእሽን ማዮይ ፔሬትዶጌ ዩኬስ

. ሆድ እቃው የተቀደደበት እያለ ልብሱ የተቀደደበት ያለቅሳል

.. እናቱ የሞተችበትና እናቱ ገበያ የሄደችበት እኩል ያለቅሳሉ

1631. ኡሎፔ ቀሬትን አፉት እጤነ

. ከሆድ ካዘኑ እንባ አይገድም

.. ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም

1632. ኡመይ ሀርኪና ግድን ላፑን ቁንአ ጢልያ ቆለርከና ጌስ

. የአሞ ወንዝ ከታች በሆነና ሰባት ቁና ዱቄት በጨመርኩበት ይላል

.. ምኞትና ጉም አይጨበጥም

1633. ኡማ ነእዮ ዴሌ አይቼስ

. የአሞን ልጅ ጐርፍ ያጫል

.. ያላቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ

1634. ኡማ ነእዮ ፑልቱዋ ነአይ አይችን ጥንቀተው ኬርን ጥንቀት ገከነው ፑልቶይ ቶኤስ

. የአሞን ልጅ የምንጭ ልጅ አጭቶ ሰርግ ለጥምቀት ተቀጠረና ጥምቀት ሣይደርስ ምንጩ ደረቀ

.. አቅምን አያውቅ

.. ጊዜ ያለው ጊዜ አይጠብቅ

.. እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው

1635. ኡረይ ተነ ሾሸይ ሜሽን ግን ሾሽይ ተነ ኡረይ ዎሬሽን ጌስ

. ሰውዬው እባብ ሊበላኝ ነው ሲል፣ እባብ ደግሞ እኔን ሰውዬው ሊገለኝ ነበር ይላል

.. የዛሬ ገበያ እንዴት ዋለ ቢሉ አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀንበር ጥልቅ አለ ይባላል

1636. ኡርቀው ሼኔትን ባነይ ቆርያ ገክዮሳ ገቴስ

. ጭቃን ከተጠየፉ አቧራ አንገት ድረስ እሚያጥለቀልቅበት ያደርሳል

.. የውሃ ጡር በድፍ ያስታጥባል

1637. ኡርቃ ሜዲዮጌ ኤረቴተ፣ ገለባ ቃጭዮጌ ሂለቴተ

. ሸክላ መሥራት ማወቅ ነው፣ ቆዳ መፋቅም ሙያ ነው

.. ማወቅ መላቅ አለማወቅ መናቅ

1638. ኡሰ ሂላ ደሮይ ጠጹዋ ቀንጤስ

. በጣም አዋቂ ነኝ ባይ ስር ይቆርጣል

.. እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት፣ እጅግ ስለት ይቆርጣል አፎት

1639. ኡሱፑን ሳቲፔ አድደ ነምሰይ ኡስታ ኮሼነ

. ከስድስት ሰዓት በኋላ የተገኘ ምግብ መበያ አያስፈልገውም

.. ከምግብ ጣፋጭ በረሃብ ጊዜ የበሉት ነው

1640. ኡስተ መ ጉቱማ ሞፐ

. አምገሀ ብላ ባዶ (ደረቅ) አትብላ

.. የነገን ነገ ይጨነቅበት

1641. ኡስያ ኡሉዋጋ ቁፊውሱ

. ጊደር የሆድዋን ትስላለች

.. ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣል

.. ልብ ያሰበውን አፍ ይናገራል

1642. ኡስያ ጉፖሳረ ልሜ ሚዝያ ጉፐደ ሚቀውሱ

. ጊደር በዘለለችበት ያረጀች ላም ዘልላ ትሰበራለች

.. አቅሙን አያውቅ

.. ከመናገር በፊት ማሰብ

1643. ኡሴ ጌዱዋ ካልደ ልምያ ሚቀደ ሀይቀውሱ፤

. ጊደርን የተከተለች ላም ተሰብራ ትሞታለች

.. አቅሙን አያውቅ

.. ከአህያ ጋር የዋለች ላም ፈስ ተምራ ትመጣለች

1644. ኡሸይ ኡሉዋገ ዮቼስ

. መጠጥ የሆድን ያናግራል

.. ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣል

1645. ኡበ ሀይቁነሣ በይስ ጊድ አሃ ዘደሉወን ዩግዮሳ ገኬስ

. ሞት ከሌለበት እሄዳለሁ ብሎ እሬሣ ቆጥ ላይ እሚያስቀ ምጡበት አገር ይደርሳል

.. ሞት የሌለበት አገር እሄዳለሁ ብሎ እማይቀበርበት ይደርሳል።

1646. ኡበ ሙሌ ቆመ አቀናረ አገዘና ጌለ ግን ዩከውሱ

. ፍጹም (በሙሉ) አቅፋ የምታድር ባል አግቢ ሲሏት ታለቅሳለች

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

1647. ኡበ በይነይ ባተን ቃቴስ

. ምንም የሌለው በጋን ያማስላል

.. ሮቃ የገዘሆን አለቃ ለምሣር አይበቃ

.. ሲወልዱ አየሁ ብላ በጠጧን ጣለች

1648. ኡበ በይነይ ጨምኡ ግን ማነ ጌስ

. ምንም የሌለው የራሰ እበላለሁ ይላል

.. የሌላት ራት ደግሞ ምሣ አማራት

1649. ኡበ በይናጌ ቡቾይ ሺጭን ማነ ጌስ

. ምንም የሌለው ጺሙ እስኪወዛ እበላለሁ ይላል

.. ቀለብ የሌለው ፀዲቅ አምጡልኝ ይላል

.. ቁልቢጥ የሌላት ድርጐ አማራት

1650. ኡበ ኤሩኩሽን ጋሼ አሻም ገውሱ

. ፍጹም የማታውቅ ጋሼ አሻም ልቀበልህ ትላለች

.. ሊበሉ የፈለጓትን አሞራ ይሏታል ጅግራ

1651. ኡበ ኤየይ በቀነ ሀንዮዴ ዶና ሀንጌስ

. ሞኝ በጥፊ ሊመቱት ሲሰነዝሩ አፉን ይከፍታል

.. ሞኝ ወሃ ሲወስደው ይስቃል

1652. ኡበዎዴ ጠምኣ ቤአናፔ እስቶ መሸይ ኬሀ ጌስ ቦረይ

. ሁልጊዜ በጨፈቃ ከመመታት የአንድ ቀን ቢለዋ ይሻላል ይላል በሬ

.. ሁልጊዜ ከመደንገጥ አንድ ጊዜ መሸጥ

1653. ኡበ ገለስ ከሎ ዩይያ ዴሺያ እሲ ዎዴ ዶርሴ ከሉዋ ቤአደ ሚጨውሱ

. ሁልጊዜ ራቁቷን የምትሄድ ፍየል አንድ ቀን የበግን እርቃን አይታ ትስቃለች

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

1654. ኡበቶ በይስ ግያረ ዞንትያሮ፣ ኡበቶ ዴማስ ግያረ ውቅያሮ

. ሁልጊዜ ጠፋብኝ የምትል የምታሸሽ ነች፣ ሁል ጊዜ አገኘሁ የምትል ሌባ ነች

.. ሞኝ አይታወቅብኝም ባይ

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

1655. ኡበቶ ጫጫ ሹክዮ ዴሸይ ዴእሽን እስቶ ጫቁወው ሹክዮ
ከነይ ዋሱወው ቤስ

. ሁል ጊዜ ለግብገ የሚያርዱት ፍየል እያለ አንዴ ለመሃላ የሚያርዱት ውሻ ለአቤቱታ ይሄዳል

.. ያልተነካ ግልግል ያውቃል

1656. ኡበይ ፐራ ቶግን አፉዋ ኦን ቤሰኔ?

. ሁሉም ፈረስ ላይ ከወጣ ማን ገደል ያሳያል

.. ችግር ነው ጌትነት ካላወቁበት

1657. ኡበፔ ጥሉዋ ቶሆይ ቤትሽን ሞጌቴስ

. ፍጹም ፃድቅ ሰው እግሩ እየታየ ይቀበራል

.. በደግነቱ ተቆረጠ አንገቱ

1658. ኡተነሰይ በይነይ እቾነሳ ኮዩስ

. የሚቀመጥበት የሌለው የሚተኛበት ይፈልጋል

.. የምትለብሰው የሌላት የምትከናነበው አማራት

1659. ኡተይ ኦይዴ ፐትን ቃጠይ ቀንታ (ኡሎ) ፐቴስ

. የተቀመጠ መቀመጫውን ሲያሽ የተንቀሳቀሰው ሆዱን ያሻል

.. መቀመጥ መቆመጥ

.. እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል

1660. ኡተይ ውሪድ ጠጹዋረ መልኤስ

. እንሰት ሊያልቅ ሲል ከነሥሩ ይጣፍጣል

.. ሰው ካልሞተና ካልሄደ አይመሰገንም

1661. ኡትኮ ጡመይ ፖኤስ

. ከተቀመጡ ጨለማው ይበራል

.. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል

1662. ኡትዮሰይ በይነይ ዝንእዮሳ ኮዩስ

. የሚቀመጥበት የሌለው የሚተኛበት ይፈልጋል

.. የምትለብሰው የሌላት የምትከናነበው አማራት



.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

.. ከእጅ አይሻል ዶማ

1671. ኡንደ አወይ ማጣና ሽምዶረኔ፣ ኤሜሬ ስምድ ቶጎረኔ፣
አድልእየን ቀጤትድ ኩንዶሮኔ

. የኡንዶ አባት አጋሰስ ከመግዛቱ፣ ወደ ጓሮ ከመጋለቡ፣ በአደይ ተጠልፎ መውደቁ

.. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሣል

.. መቼ መጣች ሙሽራ መቼ ቆረጠመች ሽንብራ

1672. ኡንዱዋሎ ባቄልያ ሻይን እጠደ ኮክን ሜሬረውሱ

. ነገር ያለባት ባቄላ ሲቆሏት ትታ ሲቀቅሏት ትንጣጣለች (ትፈካለች)

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

1673. ኡንጨው ዩክየ ናተ መረይ ዩዴስ

. ለቆጮ የሚያለቅሱትን ልጆች ጥጃ ይረግጣቸዋል

.. የተከፋ ተደፋ

.. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ

1674. ኡኔ ኦትን ኦጮይ ቦዴስ

. ተጋኘ ሲያርስ ፍልፈል ይጭራል

.. የአይጥ ምስክር ድምቢጥ

.. ከጅ አይሻል ዶማ

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

1675. ኡኖይኔ ኡዶ ሀርጌ፣ ኡት ዴንድድ ማታደን ቡክያጌ

. ወባ የረባ በሽታ አይደለም እንዲያው ብድግ ብሎ እንደ ወተት የሚንጥ

.. ቁቅም ከፈስ...

1663. ኡትዮሰ ዴሜነይ ዝንእዮሳ ኮዩስ

. የሚቀመጥበትን ያላገኘ የሚተኛበትን ይፈልጋል

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

1664. ኡትደ ክፍያ ኡሉዋ ፕትን ፓልደ ክፍያ ዶና ፕታውሱ

. የተቀመጠች ወፍ ሆዷን ስትዳብስ የበረረች ወፍ አፏን ትዳብሳለች

.. መቀመጥ መቆመጥ

.. ያልሠራ አይብላ

1665. ኡትደይ ኡኩማ ሜስ

. የተቀመጠ ዳረጐት ይበላል

.. የትዕግስት ፍሬዋ ጣፋጭ ነው

1666. ኡትድ ኦይድያ ኩሜናኔ ኡይድ ጎስያ ውርሴነ

. ቁጭ ብሎ ወንበር የማይሞላ የቅሉን ጠጥቶ አይጨርስም

.. የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

1667. ኡትድ ዎትዶበይ ኤቅድ ኤከነው ሜቲስ

. ቁጭ ብለው ያስቀመጡት ቆሞ ለመውሰድ ያስቸግራል

.. ተቀምጠው የሰቀሉት ቆሞ ለማውረድ ያስቸግራል

1668. ኡቴተይ ዜሬታ ጢፕሲስ

. መቀመጥ የዘር እህልን ያስጠብሳል

.. መቀመጥ መቆመጥ ነው

.. አፍ ስራ ሲያጣ ወዳጁን ያማል

1669. ኡቴታ ደሮይ ገልአ መሱንታ ፖቅሴስ

. የመቀመጥ ብዛት የደረቀ ቁስል ያስፍቃል

.. ስራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል

1670. ኡንእያ በንእዮ ዙንተውሱ

. የተጣበበችው የተካበደችውን ታድሃለች



1676. ኡኩማ እምዶጋ ዛር ኦይቼስ

. ጉርሻ የሰጠውን መልሶ ይጠይቃል

.. ከትንሽ ሰው ከመበደር ከትልቅ ሰው መለመን

1677. ኡክደይ ኡስ ጠይን፣ ኡትደ አዴ ኡኪታ ጨኪ ኤኬስ

. የጋገረው ሣይጠቀም የተቀመጠው ሰው ቂጣ ይገምጣል

.. ጨኸት ለቁራ መብሉ ላሞራ

1678. ኡዝያ ቁመይ ኡተ ግዶ ቤስ

. የንፉግ ምግብ እንሰት ውስጥ ይሄዳል

.. ስሱ አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

1679. ኡዝያ ቁማ ኡተይ ሚስ

. የንፉግን (የስግብግብን) ምግብ የታገሰ ይበላል

.. ንፉግ ለግሶ ቢሰጥ እጁ ይንቀጠቀጥ

.. አጎንብሶ የሚበላን ተኝተህ ቀላውጠው

1680. ኡዝያ ከተይ ኡተ ግዶን ውሬስ

. የንፉግ እህል እንሰት ውስጥ ያልቃል

.. እብድ የያዘው መልክ አይበረክትም

.. የጋን መብራት

1681. ኡዜ በርባ ኦይቅድ ሃይቁስ

. ንፉግ የራሱን ይዞ ይሞታል

.. ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል

.. ስሱ አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

1682. ኡየነ ማተይ ማነ ጢልያን ጉኬስ

. የሚጠጡት ወተት እሚበሉበት ዱቄት ላይ ይፈሳል

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

.. በድንገት አህያ ከጅብ ቤት

1683. ኡዱንጤ ኡትድኔ ዴጤነ ዴንድድኔ ከውዬነ

. ዝንብ ሰው ላይ ቢቀመጥም አይከብድም፣ ቢነሣም አይቀልም

.. ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም

1684. ኡዱፑን ሳትያ ኔ ጋጭዶባ ተ እስ ሳትየን ሙነቀይስ ጌስ እረይ

. አንተ ዘጠኝ ሰዓት የፈጨኸውን እኔ በአንድ ሰዓት አቦካለሁ
ይላል ዝናብ

.. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

1685. ኡዶ አሾ ግን ዶርን ገንጀ ግዴስ

. ጥሩ ስጋ ነው ብለው ሲያሞግሱት የማይሆን ቅጠል ሆኖ ተገኘ

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

1686. ኡፈይሰይ እረን ጨወዬስ

. ደስታ (የምሥራች) በዝናብ ላብ ያመጣል

.. በድንገት አህያ ከጅብ ቤት

1687. እ ሼምፖይ ሻጮ ጌስ ዘልአንቸይ

. ነፍስ በከረመ ይላል ነጋዴ

.. የበላውን ያብላላዋል፣ የለበሰውን ይበርደዋል

1688. እ ኡበ አሰን ቆዴቲ?

. እርሱም ከሱው ተቆጥሮ?

.. ቁቅም ከፈስ ተቆጠረች

1689. እመታ ኢተው በደላ ሻሻ

. ለመጥፎ እንግዳ የበቆሎ ቆሎ ይቀርብለታል

.. ለጠላት እሾህ አሜከላ ለወዳጅ የማር ወለላ

1690. እምን ሚኬ ግየይ ዝንእን ውቅ ሜስ

. ቢሰጡት አልበላም ያለው ከተኙ በኋላ ሰርቆ ይበላል

.. ሲስሟት ጥላ ሲስቧት

1691. እምን ሚኬ ጊደይ ከይሶት ሜስ

. ተሰጥቶት አልበላም ያለው ሰርቆ ይበላል

.. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሣል

.. ሲስሟት ትታ ሲስቧት

1692. እረው ጌለይ ከውዋ ግቬስ

. ለዝናብ የገባ እራት ያድላል

.. ደፋር ወጥ ይሰራል

.. አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል።

1693. እረይ ኔነ አውን ዋድዴ ጊን ቱተን ያግን ዎን አሶ ብን ኔነ ወዴነን አጊ?

. ዝናቡ የት መታህ ቢለው ቱታ ብል ድሮውንስ እቤቱ ሄደህ ሊተውህ ነው?

.. ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ

1694. እረይ ዴእሽን ገበይ ሜሌስ

. ዝናብ እያለ የዐደይ ወራት እህል ይደርሳል (ይደርቃል)

.. ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም

1695. እረይኔ፣ ኤረይኔ ይድ ኤሬቴስ

. ዝናብና አዋቂ ሲመጡ ያስታውቃሉ

.. ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት፣ እንግዳ ባይምጣ ሁሉ ሴት

.. ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀደዳል

1696. እራ ሱሰይ አይ ቀቾ ግን፣ ፐርሶ ዶነይ አይ አዶ ጌስ

. የዝናብ ወፍቾ ምን ልሰር ሲል፣ የጠላ አፍ ምን ልናገር ይላል

.. ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣል

.. መጠጥና እብደት የልብን ያናግራል

1697. እራስ ጌልደ እመተይ ከሆ ግሸነው ፐለሜቴስ

. ለዝናብ የገባ እንግዳ ራት ላድል ብሎ ይከራከራል

.. አያገባው ገብቶ ላያወዛው ተቀብቶ

.. አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል

1698. እረው የይደ ብተንያ መችዮ ትየ አሰንቸይ ኤኬስ

. ለዝናብ የፈራውን ሰው ሚስት እሸት ያመረተ ያገባታል

.. ያለው ይበላል የሌለው ያፈጣል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

1699. እሰረ ዴርያፔ ጉምቡሩዋ ማንሳ ዱልየን ዴእየ ከፍዮ

ምዝያጌ ተነ ዩጌነ

. ከኢሣራ ጋር የተነሣችውን ቅምቡርስ ማንሣ ዳር ያለችውን ወፍ የሚያበላ እኔን አይጥለኝም

.. ጫን ያለው ኮርቻውን ተሸከም ያለውን ስልቻውን

.. አሞራ ቀላቢ አምላክ አለልኝ

1700. እሱዋ ሶን ሼንዴረይ ፖሬስ እሱዋ ሶን ሼምፖይ ፖሬስ

. አንዱ ቤት ገንፎ ይንፈቀፈቃል፣ አንዱ ቤት ነፍስ በጣር ተይዞ ኮርኮር ይላል

.. አንዱ በጠኔ፣ አንዱ በቁንጣን ይሞታል

1701. እስ መቼ ጎደይ ሊቄነን ሚኬ ጌስ

. አንድ ሚስት ያለው ተፈጭቶ ካልደቀቀ አልበላም ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1702. እስ መቼ ጎዳይ ቶኬነን ቢኬ ጌስ

. አንድ ሚስት ያለው ሳትሸከሙኝ አልሄድም ይላል

.. ያለአንድ የሌላት ጥርስ በዘነዘና ትነቀስ

1703. እስ ምተ ማጼነይ ጎዳ አሳ ጌስ

. አንድ እንጨት የማያግገ ግድግዳውን ሰፋ አድርግ ይላል

.. በቅሎ ግዙ ግዙ አሞሌ ላያግዙ

1704. እስ ሚዜ ጉሶይይ ውድያ ሚዛ ሞሬስ

. የአንዲት ላም ቅዘን የበረቱን ከብት ያበላሻል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

.. በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል

1705. እስ ሚዜ ጉሶይ ውዴ ሞሬስ

. ያንዲት ላም ቅዘን ብዙ ላሞችን ያበላሻል

.. በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል

1706. እስ ሚዜ ጎደይ ማታ ጥጊነን ኡይኬ ጌስ

. አንድ ላም ያለው ትኩስ ወተት ካልተጣራ አልጠጣም ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1707. እስ ሚዜ ጎደይ ማት በይነን ሚኬ ጌስ

. አንድ ላም ያለው ወተት ከሌለ አልበላም ይላል

.. አንድ ጣት በቆማጣ ቤት ብርቅ ናት

1708. እስ ሚዜ ጎደይ ጉቱማ ሚኬ ጌስ

. አንድ ላም ያለው ደረቁን አልበላም ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1709. እስ ሶን ሼንዴረይ ፖሬስ፣ እስ ሶን ሺምፖይ ፖሬስ

. አንድ ቤት ገንፎ ይንፈቀፈቃል፣ አንዱ ቤት ነፍስ ይንፈቀፈቃል

.. ያለው ይመዛል የሌለው ይፈዛል

1710. እስ ቀረይ ሜንታ ከጪያን ገልባ ከቂስ፣ ሁንኮ ቀረይ ቀስ ዎት ኤኪስ

. አንድ ጐበዝ ጐሽ ቀንድ ላይ ቆዳ ይሰቅላል፣ ሌላው ጀግና ደግሞ ያወርዳል

.. ከጐበዝም ጐበዝ ከጀግናም ጀግና አለ

1711. እስ በጋ ኦዶይ በሽን፣ እስ በጋ አለይ በሼስ

. አንድ ወገን ወሬ ያጠፋል፣ አንዱን ወገን ጦርነት ያጠፋል

.. ጦርነት ከፈታው ወሬ የፈታው

1712. እስ ብረተይ ጊሬነ፣ እስ ጢፈይ ኤጤነ

. አንድ የብረት ጌጥ አይጮህም፣ አንድ ትንታግ አይነድም

.. አንድ ሰው አይፈርድም አንድ እንጨት አይነድም

1713. እስ ቶሁዋ ጎደይ ሆንጦይ መተ ጌስ

. ባለአንድ እግር እንጦጦ ቅርብ ነው ይላል

.. አንካሳ በልቡ ኢየሩሣሌም ሀሣቡ

.. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ

1714. እስ አሳረ ሚኬ ጊያጋ፣ አቸሹ አሣረ ምዜስ

. ከአንድ ሰው ጋር አልበላም ያለውን ከአምስት ሰው ጋር ያበላዋል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

1715. እሲ አቻ ጎደይ ሜሬሰይ ጢሌ ጌስ

. ባለአንድ ጥርስ ፈንድሻ ዱቄት ነው ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1716. እስ አይፌ ጎደይ ኩሳሞይ አኔ ጌስ

. ባለአንድ አይና ሳማ የታለ (ምናባቱ) ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1717. እስ ኡረይ ፐጠ ዴእዮ ኬነን ላፑንቶ ዱሬቴስ ላፑንቶ መንቄስ

. አንድ ሰው በህይወት ሲኖር ሰባቴ ከብሮ ሰባቴ ይደኸያል

.. እድሜ መስተዋት ነው

.. መከራን የቻለ አሸናፊ ነው

1718. እስ ኡታ ቶክደይ ሀጋ ኡባ ዋተኔ ጌስ

. አንድ እንሰት የተከለ ሰው ይህን ሁሉ እንሰት ምን ላድርግ ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1719. እስ ኡቴ ጎደይ አንገለይ አኔ ጌስ

. ባለአንድ እንሰት ቡላው የታለ ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1720. እስ ኡቴ ጎደይ ዎዜነን ሚኬ ጌስ

. ባለ አንድ እንሰት ሣታፈራ አልበላም ይላል

. አንድ እንሰት ያለው ሳታብብ አልበላም ይላል

.. ያለአንድ የሌላት ጥርት በዘነዘና ትነቀስ

1721. እስ እጮይ ጣመ፣ እስ በርሶይ ሀንደ

. አንድ ክርን በሽታ፣ አንድ ጉርሻ መድሃኒት ነው

.. ከምንም ትንሽ ያለው ይሻላል

.. ያጠፋ ይከሣል የወለደ ይልሳል

1722. እስ አሰንቾይ ፐራ ሸምን ላፑን አሰንቾይ ሊሱዋ ኦይኬስ

. አንድ አሽከር ፈረስ ሲገዛ ሰባት አሽከሮች አለንጋ ይይዛሉ

.. በእውሮች መሀል አንድ አይናው ንጉስ ነው

1723. እስ ዱሌ ጎደይ ዱቡሸይ ተው ጉጤስ ጌስ

. ባለአንድ ቂጥ ሜዳው (ቀየው) ያንሰኛል ይላል

.. አንድ ያላት እንቅልፍ የላት

1724. እስቶ ከሆይ ከይሱወው ኤፈስ

. ያንድ ቀን ራት ማጣት ለሌብነት ያስኬዳል

.. ያጣ ሰው ይሉኝታ የለውም

1725. እስነ በይነይ ግያ ፔኤነ

. ምናምን የሌለው ከገበያ አይቀርም

.. ውሻ ሣይቸግረው ገበያ ይሄዳል

1726. እስንን ሾጩነይ ተሙ ጉፌ ኦይቂስ

. በአንድ የማይመታ አስር ዱላ ይይዛል

.. የፈሪ ዱላ አስር ነው

1727. እሶ ዎረይኔ ኩሼ ስንግ ስዩስሽን

. ትኳን የገደለም እጅ ያሸት የለ እንዴ?

.. ጥቀመኝና ልጥቀምህ

1728. እሶይ ኦት ፔአሳፔ ጮረይ ከንቶሰይ ኬሀ

. አንዱ አርሶ ከዋለበት ብዙሃኑ ረግጦ ያቋረጠበት ይሻላል

.. ድር ቢያብር አንበሣ ያስር

.. ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ

1729. እሸነይ ምችነይ በይነ ቁጤ ሞቶ፣ አቦይ ደቦይ በይነ ግየ ሳም

. የወንድም የእህት ልጅ የሌለበት የማይሳካ ሙግት፣ አጐት ዘመድ የሌለበት የገበያ ጥም

.. ዘመድና መድሃኒት የተቸገሩ ዕለት

1730. እሸይ መጉልሣ ሞርን ምችያ ዬለተውሱ

. ወንድም ጦር መስበቅን ሲያበላሽ እህት በተቀመጠችበት ታፍራለች

.. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሣል

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

1731. እሸይ ምችዮ አይቅድ ዋሰ ግን አለነ ኔ አይቀዴሰ ተ ኦስ ዋሶ ገውሱ

. ወንድም እህቱን ሊዳራት ይዞ ጩሂ ቢላት የምትደርስልኝ አንተ ያዝከኝ ለማን ልጩህ አለች

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

1732. እሸይ ምንን ምችያ ጬቀውሱ

. ወንድም በበረታ እህት ትፎክራለች

.. የጐበዝ ወዳጅ ታስታውቃለች፣ አፋፍ ላይ ቆማ በለው ትላለች

1733. እሸይ በይነ ኡራ ኦኔ ወዴስ

. ወንድም የሌለውን ሰው ማንም ይደበድበዋል

.. ወጥና ወንድም ማስፈራሪያ ነው

.. ወንድም ለግርግርታ ጋሻ ለመከታ

1734. እሸ ነእኔ ምቼ ነእኔ ነአ፣ ዬሎ ነአይ ጉድያ ተመ፣ ሸሎይ

በይነ ኡር ህየሰ

. የወንድም የእህት ልጅ እንደ ራስ ልጅ ነው የወለዱት ልጅ እንደሚያቃጥል እሣት ነው፣ ገንዘብ የሌለው ሰው ድሃ ነው

.. ገንዘብ የጠፋበት ብዙ ሃጢአት አለበት

1735. እሸ ቆፔነ ሶሆ ምችያ ቆፐውሱ

. ወንድም በማያስብበት አቅጣጫ እህት ታስባለች

.. የናት ሆድ ዝንጉርጉር

.. ፍየሏ ወዲያ ቅዝምዝም ወዲያ

1736. እሸ በይነ ዞኩዋ ኦኔ ይምፔስ፣ ጨለይ በይነ ዞኩዋ አዋይ ጡጌስ

. ወንድም የሌለውን ሰው ጀርባ ማንም ይጐስማል፣ ድብዳብ የሌለበትን ከብት ጀርባ ፀሐይ ይመታል

.. ሰው ያለቤቱ ያንሳል ጉልበቱ

1737. እሸ በይነይ እሸሌነ እሸተም በይነይ ግያ ጌሌነ

. ወንድም የሌለው አይደላውም አምሳ የሌለው ገበያ አይገባም

.. ከሌለህ የለህም

.. ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ

1738. እሸ እሸ ገዴን እር ቡኮፖ ጌስ

. ወንድም በወንድሙ መሬት ላይ ዝናብ አይዝነብ ይላል

.. ጠላት ይወጣል ከቤት

.. የሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ

1739. እንቴነ ግዮ አሰኔ ፑዴ ሱግዮ ሹችኔ እሰኖ

. አንቱ የሚሉት ሰውና ወደላይ የሚገፉት ድንጋይ አንድ ናቸው

.. የማይችሉት ድንጋይ ሲያወጡት ደረት ሲያወርዱት ጉልበት

1740. እንጂ በደለ ዖዴ

. ምቾት የበቆሎ ጊዜ ነው

.. ለካህን ጥምቀት ለገበሬ ግንቦት

1741. እንጠርሳ ሊቅደይ ጨርሻረ ከንቴስ

. ምላሱን ያለሰለሰ በቡቃያ መሃል ያልፋል

.. ፍየል በለስላሳ ምላሷ እሾህ ትበላለች

.. መልካም ምላስ ቂጣን ታበርዳለች

1742. እከ ቃልቼ እከ ሺሼኔ

. እሱም ቃልቻ እሱም የማያስጠጋ

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

1743. እከ ኡተ በውከ ጉተ

. እሱም እንሰት ለራሱም ትንሽ

.. አይጠቅም ጋሻ ቂጥ ያስወጋ

1744. እክሳመ ከነይ ሞዶ ጊሽን ሀይቂስ

. ፀጉራም ውሻ ወፍራም ነው ሲባል ይሞታል

.. ፀጉራም ውሻ ወፍራም ነው ሲባል ይሞታል

1745. እክሳመ ዶርሰይ ሞዶ ጊሽን ሀይቂስ

. ፀጉራም በግ ወፍራም ነው ሲባል ይሞታል

.. ፀጉራም ውሻ ወፍራም ነው ሲባል ይሞታል

1746. እዛው ቀንተይ ፓጨናፔ ላፑን ለጌ ፓጮ ጌስ

. የባለቤቱ ልብ ከሚታዘብ ሰባት ጓደኛ ይታዘብ ይላል

.. ልብ ሲያውቅ ገንፎ ያንቅ

1747. እድመናረ በእን ሻቴስ ገውሱ

. በኋላ የምታቅፍ ሲያዝላት አስጠላኝ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

1748. እጥዮ ናቱ ሽየይ ገዴፔ ይድ ጥንቂስ

. የሚጠሉት ልጆች አር ከውጪ ይሸታል

.. የምትጠላው ሰው ፊሱ ሆዱ ውስጥ ሣለ ይሸታል

1749. እጥዮ ኤጩርያ ሰምፓ ግአውሱ

. የሚጠሏት አይጥ መሶብ ላይ ትወጣለች

.. ብላ ሣይሉት ከወጡ አውጡልኝ

1750. እጨተይ ግጨቱዋ ገርጨስ

. ማጣት ነጠላ (ቡልኮ) ያስውሣል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

1751. እፍተይ መቀሽን ዋጣጣ ቃሾ ጋዬ ሹለሽን ቱለይ ቁፎ

. መዝጊያው አገዳ ሆኖ ወጥሮ ማሰር፣ ትምባሆው ጠውላጋ ሆኖ በኃይል ማሳል

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

1752. እፍተይ መቀሽን ዜጾት ቀቼስ

. መዝጊያው አገዳ ነው ግን ወጥሮ ያስራል

.. አቅሙን አያውቅ

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

1753. እፍታ ሾሮስ እምድ በ ሁጽየው ጎደርየን ሜቴቴስ

. መዝጊያውን ለጎረቤት ሰጥቶ ለራሱ በጅብ ይበላል

.. ሞኝ ሰው ራቱን ለሰው ሰጥቶ ለራሱ ጦሙን ያድራል

1754. ኢስድ ኢተ ጋኔ፣ ጡንቅ በርስድ ግልቀ ጋኔ

. አስከፍቶ ክፉ ሊባል ወይስ ቆንጥሮ አጉርሶ ከሲታ ሊባል ነው?

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

1755. ኢስድ ኢተ ጌቴስ፣ ሜለ አይሲድ አዴ ዮረ ጌቴስ

. አስከፍቶ ክፉ ይሉታል፣ ጾሙን አሳድሮ ሰውየው ሆዳም ነው ይሉታል

.. ተናግሮ አናገረኝ ይወደኝ ይመስል፣ ሄዶ ተናገረ የላኩት ይመስል

1756. ኢተ ማስ ቁማፔ ኤሬት!

. መጥፎ ምግብ በላሁ አጥሚት!

.. ማር ሽጦ ምን ይገዟል ጠጅ ጠልቶ ምን ይወዷል

1757. ኢተ ሜቶይኔ፣ ጡመ ዴሬቀይኔ እሱዋ

. ክፉ ችግርና የጨለማ ግልምጫ አንድ ነው

.. ችግርና መከራ አይን ለአይን ፍጥጥ

1758. ኢተ ቁመይ ናኡ ኬሬ ከጤስ

. የማይረባ ምግብ ሁለት ጣባ ይሰራል

.. ያልፈለጉት እንግዳ ሰባት ቀን ያድራል

1759. ኢተ ኡረይ ኤሬነ አግያ ካሌት ኤፊድ፣ ግዶ ገቲድ አግ ቤስ

. ክፉ ሰው የማያውቁት መንገድ አስከትሎ ወስዶ እመሃል ሲደርስ ይተዋል

.. ሰው ማመን ቀበሮ ነው

1760. ኢተ ኡራ ኡሉዋ ኮሶይ ከንቴነ

. የክፋን ሰው ሆድ ኮሶ አይዘልቀውም

.. ክፉ የከፋ ዕለት ቢስ የባሰ እለት

1761. ኢተ ጎይ ሎኦ ግዴስ

. መጥፎ ያሉት ጥሩ ይሆናል

.. ክፉ ሰው ለክፉ ቀን ይሆናል

1762. ኢ.ተባ ሚድ ተ ኡሉዋ ጋናፔ ሜለ አቅድ ሰሮ ዴምኮ ሎኦ

. አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት፣ ጦም ውሎ አድሮ ደህንነት ይሻላል

.. አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት፣ ጦም ውሎ ጦም አድሮ ጥሩ መሸመት

1763. ኢ.ተይ ኢ.ስ ጨዩስ

. ክፉ አስከፍቶ (አምርሮ) ይሳደባል

.. ክፉ ይነካል በክንፉ

1764. ኢ.ተይ ኢ.ስን ኬሀይ ዋሴስ

. ክፉ ሰው ሲያጠፋ ደግ ሰው ዋስ ይሆናል

.. ሰው ይውደድህ ድንጋይ ይጫንህ

1765. ኢ.ተይ ኬሀይ ዴኤስ ጨዋ ዘንዛ ዶጎፐ

. ክፉ ደግ አለና የላብ መጥረጊያ አትተዪ (አትዘንጊ)

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

1766. ኢ.ተይ ውሮ ግን ዩሌትድ አቂስ

. መጥፎ እለቅ ሲሉት እየተወለደ ያድራል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

1767. ኢ.ተይ ዝንእድ ቀኬስ

. ክፉ (መጥፎ) ተኝቶ ይረግጣል

.. የሰው ግብሩ አይለየው እስከ መቃብሩ

1768. ኢ.ታረ ምን እቂስ፣ ሰንታረ ፐላረ ምን ቡቂስ

. ከመጥፎ ጋር ከበሉ ቁርጠት ያመጣል፣ በጉመንና በአይብ ቢበሉ ያንቆራጥጣል

.. አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት፣ ጦም ውሎ ጦም አድሮ ጥሩ መሸመት

.. ከጮማ ብስና ጉመን በጤና

1769. ኢትድ አይዮ አዋ ዎሬስ፣ ከሂድ ግየን ቆጫን ዎዴስ

. ሲከፋ እናትን አባትን ይገላል፣ ሲበጅ (ሲቀና) ከቆጪ ከገበያ ይተርፋል

.. ያለው የእንጀራ እናቱን ተገዛካር ሲያወጣ የሌለው የናቱን ያስታጉላል

1770. ኤልያ መችያ ኮልያ ዩለውሱ

. የምትቀብጥ ሴት ባለአንድ ዘር ትወልዳለች

.. አጉል የጀነነ መውደቂያው አያምርም

1771. ኤልያ መችዮ ቆጦይ ሰኪስ፣ ኤጨርያ መችዮ ቁንጦይ ጩሌስ

. የምትቀብጥ ሚስት ራስ ምታት ያማታል፣ የአይጥን ሚስት ኮቸሮ ያንቃታል

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

1772. ኤሌልየ ሜጠይ አውለሽያ (ኩንትያ) ሚገዞ ዩሴስ

. የሚቸኩል «ሜፃ» (ዘር) እርጉዝ ላም ያልባል

.. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሣል

1773. ኤሌልየ ኩትያ ሰምሰውሱ

. የምትቸኩል ዶሮ እንቁላሉን ታበሰብሰዋለች

.. የቸኮለች አፍሣ ለቀመች

1774. ኤሌልደይ ሃታ ኤሬታ ኤኪስ

. የሚቸኩል የውሃ ሙቅ ይደርሰዋል

.. የጅብ ችኩ\ ቀንድ ይነክሳል

1775 ኤሌሶይ ገሃ'ኦን ገቴስ

. ችኮላ እንዲዘገ' ያደርጋል

.. የቸኮለች አፍሣ ለቀመች

1776. ኤሌትደይ ሜኤስ

. የቀበጠ ይሰበራል

.. ካልጠገቡ አይዘሉም ካልዘለሉ አይሰበሩም

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

1777. ኤረው አድዮጌኔ ቀረው አድዮጌኔ ጦን ኤሬነ

. ለአዋቂና ለጐበዝ መንገር አያስቸግርም

.. ለአንበሳ አይመትሩም ለአዋቂ አይነግሩም

1778. ኤረይ ኤራ ጭሜስ ከነይ ሾቀን ዝንኤስ

. ብልህ ብልህን ያታልላል ውሻ ማሳ (ቆረን) ላይ ይተኛል

.. ከብልህም ብልህ ከጀግናም ጀግና አለ

.. ብጥለው ገለበጠኝ

1779. ኤረይ ኦደነ ጊሽን አሰይ ኤራ ኦዱዋ ድግኮ ኤራስ ኡሎይ ሰኪስ

. አዋቂ ልናገር ሲል አትናገርም የተባለ እንደሆነ ሆዱን ያመዋል

.. እውነት ትመነምናለች እንጂ አትሞትም

1780. ኤረይ ጉቱዋነ ኤየይ ቦአነ

. እውቀት በልጅነት (በጉተና) ሞኝነት በሽምግልና

.. እወቅ ያለው ባርባ ቀኑ አትወቅ ያለው ባርባ ዘመኑ

1781. ኤረይደ ጭመ ጌለደ ጎየደ ሀናስ ገውሱ

. አውቃ ሽማግሌ አግብታ አብጄ ነው ትላለች

.. ለማያውቁሽ ታጠኝ

1782. ኤራ ዞርዮጌኔ ቀራ ሌፍዮጌኔ እሱዋ

. ብልህን መምከርና ስለትን መሳል አንድ ናቸው

.. ለብልህ አይነግሩም፣ ለአንበሳ አይመትሩም

1783. ኤራ ደሩዋፔ ዱጥን ስምየ ጎሸይ ኪሀ

. እውቀት ከሚያበዛ ሲያስሩት የሚመለስ እብድ ይሻላል

.. እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት እጅግ ስለት ይቀዳል አፎት